# የቱሪዝም ሚኒስቴር

1) የቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

I. የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የህግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

II. በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

III. የሀገሪቱን የቱሪዝም እና የኢኮ-ቱሪዝም አለኝታዎችና መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

IV. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

V. አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ ያደርጋል፣ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

VI. የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ይፈጥራል፣ የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፤

VII. ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ እንዲያድግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

VIII. የቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

IX. የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

X. በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲመሩ የማደረግ ስራን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርፃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

XI. የሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በአለማቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

XII. የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

XIII. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

www.amanuela.com

XIV. ሥልጣኑ በግልጽ በሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ህግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

XV. ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር በመፍጠር ይሰራል፤

XVI. የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፤

XVII. ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የሚቋቋመውን የቱሪዝም ፈንድ ያስተዳድራል፤

XVIII. የግል ዘርፍ አካላትንና የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በህግ የሚደራጅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

XIX. የቱሪዝም ዘርፍ መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት ኣካውንት በአገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሃድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

**2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ቱሪዝምን የሚመለከቱ እና ለቱሪዝም ኢትዮጵያ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።**

## ለቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

**የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል:-**

I. የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣

II. የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን።

www.amanuela.com